

### እርስዎ ወይም የልጅዎ አቅራቢ ልጅዎ ኦቲዝም አለበት/ባት ብለዉ ጠርጥረዉ ይሆን

# ኦቲዝም ስፔክትረም ዲስኦርደር?

## ኦቲዝም ምንድን ነዉ?

ኦቲዝም ወይም ኦቲዝም ስፔክትረም ዲስኦርደር (ኤኤስዲ) ማለት ከማህበራዊ፣ ግንኙነት፣ እና ባህሪያዊ ችግሮች ጋር ሊያያዝ የሚችል የነርቭ እድገት እክል ነዉ። ኦቲዝም ምርመራ የተደረገላቸዉ ልጆች ኦቲዝም ከሌለባቸዉ ሰዎች ጋር በተለየ መልኩ የመግባባት፣ መስተጋብር፣ ባህሪይ፣ እና የመማር ሁኔታ ይኖራቸዋል። እርስዎ  የ **ሴንተርስ ፎር ዲዚዝ ኮንትሮል ኤንድ ፕሪቬንሽን (ሲዲሲ)** ድረገጽ በመጎብኘት **ኦቲዝም እንዴት ትርጉም እንደሚሰጠዉ የበለጠ ማወቅ ይችላሉ**።

## ኦቲዝም ምን ያህል የተለመደ ነዉ?

ሴንተርስ ፎር ዲዚዝ ኮንትሮል ኤንድ ፕሪቬንሽን(ሲዲሲ)ከ  44፣ 8-ዓመት ልጆች በ 1 ላይ ኦቲዝም እንዳለባቸዉ ተለየቶ እንደታወቀ ግምት ያስቀምጣል። የበለጠ ለማወቅ እርስዎ የሲዲሲ ኦቲዝም እና እድገት እክል መቆጣጠሪያ ኔትወርኮች **2021 ማህበረሰብ ሪፓርት** መመልከት ይችላሉ።

## ኦቲዝም እንዴት ይመረመራል?

የኦቲዝም ምርመራ የሚደረገዉ የእርስዎ የእርስዎን ልጅ እድገት ገለጻ፣ የእርስዎ ልጅ ታሪክ ግምገማ እና በእርስዎ ልጅ ዋና እንክብካቤ አቅራቢ እና ኦቲዝም ኤክስፐርት በኩል የተወሰኑ ባህሪያቶች ምልከታ ማድረግ ላይ ተመስርቶ ነዉ። እርስዎ የአሜሪካ ፔዲያትሪክስ አካዳሚ ጽሁፍን በማንበብ የበለጠ ማወቅ ይችላሉ፣**"ኦቲዝም እንዴት ይመረመራል?"**

## የኦቲዝም ምርመራ መስፈርቶች የሚያካትቱት:

- ☑ በማህበራዊ ግንኙነት እና መስተጋብር ላይ የሚታዩ ችግሮች የገደቡተ
- ☑ ወይም ተደጋጋሚ ባህሪያቶች ወይም ፍላጎቶች

DC AUTISM COLLABORATIVE

## የኦቲዝም ቀዳሚ ምልክቶች ምንድን ናቸዉ?

አብዛኞቹ ኦቲዝም ያለባቸዉ ልጆች ከተዘረዘሩት ባህሪያቶች ዉስጥ በተወሰኑት፣ነገር ግን በሁሉም አይሆንም፣ ተሳትፎ ሊኖራቸዉ እንደሚችል መገንዘብ ጠቃሚ ነዉ። ሲዲሲ የኦቲዝም ምልክቶች ዝርዝር አለዉ  በቀጥዩ ሊንክ ማግኘት ይችላሉ **እዚህ ጋር**።

የአሜሪካ ፔዲያትሪክስ አካዳሚ ተመሳሳይ የሆነ ዝርዝር አለዉ፣ **"የኦቲዝም ቀዳሚ ምልክቶች ምንድን ናቸዉ?"** ይህም ኦቲዝም ያለበት ልጅ ከ መደበኛ መልኩ እድገት ካለዉ ልጅ ጋር የሚኖረዉን ልዩነት እንዴት መለየት እንደሚቻል ያካትታል። የኦቲዝም አሳሽ ያጎለበተዉ **ህጻን ልጅ አሳሽ መመልከቻ መጽሃፍ: 16 ቀዳሚ የኦቲዝም ምልክቶች በ 16 ወራቶች**።

የኬኔዲይ ክሪገር ኢንስቲቲዩት ያጎለበተዉ ነጻ **9-ደቂቃ ቪዲዮ አጋዥ ስልጠና** ቀዳሚ የኦቲዝም ምልክቶች መለየትን ያሻሽላል። አጋዥ ስልጠናዉ ምንም አይነት ኦቲዝም ምልክቶች ያልታዩባቸዉ ታዳጊዎችን ቀዳሚ የኦቲዝም ምልክቶች ከታዩባቸዉ ጋር የሚያነጻጽሩ 6 ቪዲዮ ክሊፖችን አካቷል።

## ኦቲዝም ከጠረጠርኩኝ፣ ምን ማድረግ አለብኝ?

እርስዎ ኦቲዝም የጠረጠሩ ከሆነ፣ ለቀጣይ እርምጃዎ ብዙ አማራጮች አሉ። በአብዛኛዉ ብዙ መንገዶችን በተመሳሳይ ጊዜ መከተል ጠቃሚ ነዉ። ይህም ቀደም ብሎ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት ወይም ትምህርታዊ ግምገማዎች (ጠንካራ አጀማመር ወይም ቀዳሚ ደረጃዎች) መፈለግን ያካትታል። በሕክምና መዋቅር ዉስጥ ግምገማዎችን ይፈልጉ። ከልጅዎ ዋና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ስለ እነዚህ ምርጫዎች ይነጋገሩ። የልጅዎ ዋና እንክብካቤ አቅራቢ "ይጠብቁ እና ይመልከቱ" ብሎ ከነገርዎት፣ ነገር ግን እርስዎ ምክሩ የመረጋጋት ስሜት ካልፈጠረልዎት፣ እርስዎ **ጠንካራ አጀማመር** ወይም **ቀዳሚ ደረጃዎች** **በራስ-ጥቆማ** ማድረግ ይችላሉ።



## ቀደም ብሎ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት/ ትምህርታዊ ግምገማዎች

በ **ኢንዲቪጂዋልስ ዊዝ ዲስኤቢሊቲስ ኤዱኬሽን አክት (አይዲኢኤ) ክፍል ሐ** እና **ክፍል ለ**፣ በመመራት **ጠንካራ አጀማመር** እና **ቀዳሚ ደረጃዎች** በኮሎምቢያ ዲስትሪክት  ዉስጥ ለሚገኙ ሁሉም ቤተሰቦች በነጻ የሚሰጡ ናቸዉ። ልጆች ለአገልግሎቶች ብቁ መሆናቸዉን ለይቶ ለማወቅ ግምገማ ይደረጋል።

- ☑ ከዉልደት እስከ 2 ዓመታቶች፣  10 ወራቶች ለሆናቸዉ ልጆች ፣ **ጠንካራ አጀማመር** ከ 1-5 በሚገኙት የእድገት ክፍሎች ላይ 25%  መዘግየት የሚኖር ከሆነ በ ኢንዲቪጂዋላይዝድ ፋሚሊይ ፕላን(አይኤፍኤስፒ) አገልግሎቶችን ይሰጣል። ምንም እንኳን ልጆችን ኦቲዝም አለባቸዉ ብለዉ የሚመረምሩ ወይም የሚመድቡ ባይሆንም፣ ኦቲዝም ያለባቸዉ ብዙ ልጆች የሚያስፈልጋቸዉን ጠቃሚ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፣ ለምሳሌ የንግግር ቴራፒ፣ ሙያዊ ቴራፒ፣ እና ተግባራዊ የባህሪ ትንተና ናቸዉ።
- ☑ 2 ዓመታቶች፣ 8 ወራቶች እስከ 5 ዓመታቶች፣ 10 ወራቶች ለሆናቸዉ ልጆች፣ **ቀዳሚ ደረጃዎች** ግምገማዎች በአይዲኢኤ-ተለይተዉ የሚታወቁ 14 እክሎች ኦቲዝምን ያካትታሉ ልጆች በአንዱ ላይ መስፈርቱን እንደሚያሟሉ ለይቶ ለማወቅ ጥቅም ላይ ይዉላሉ። ቀዳሚ ደረጃዎች ኢንዲቪጂዋላይዝድ ትምህርት ፕላን(አይኢፒ) የሚፈጥሩ እና የሚያዙ ይሆናል። አይኢፒ አገልግሎቶች በዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ዉስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸዉ።

## በሕክምና መዋቅር ስር የኦቲዝም ግምገማዎች

ልጆች ሁሉን አቀፍ የኦቲዝም ምርመራ በሕክምና አቅራቢ(ፔዲያትሪሺያን፣ ሳይኮሎጂስት፣ ወይም ሌላ የሕክምና ባለሙያ) በኩል በሕክምና መዋቅር ስር ማግኘት ይችላሉ። እነዚህ ግምግማዎች አብዛኛዉ ጊዜ ላይ በልጅዎ የጤና ኢንሹራንስ የሚሸፈኑ ናቸዉ። አቅራቢዎች የእርስዎን የልጅዎ እድገት፣ የእድገት ታሪክ፣ ምልከታዎች፣ እና ግምገማ ገለጻ በመጠቀም የእርስዎ ልጅ **ዲኤስኤም—5 ምርመራ መስፈርት ለ ኤኤስዲ**. ለይተዉ የሚያዉቁ ይሆናል። የእርስዎ ልጅ እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ፣ አቅራቢዉ ለእርስዎ ልጅ **የኦቲዝም ሕክምና ምርመራዎች** የሚሰጥ ይሆናል።

## በኦቲዝም ሕክምና ምርመራ እና ትምህርታዊ ምድቦች መካከል የሚገኙት ልዩነቶች ምንድን ናቸዉ?

አብዛኛዉ ጊዜ ላይ የ **ዲኤስኤም—5 ምርመራ መስፈርቶችን** በመጠቀም በሕክምና አገልግሎት መዋቅር ስር በሕክምና አቅራቢ የሚደረግ፣ የኦቲዝም ሕክምና ምርመራ ሁልጊዜ ለቀደመ ጣልቃ ገብነት/የተለየ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ መሆን አያስችልም። የኦቲዝም ሕክምና ምርመራ ልጆች በእነርሱ የሕክምና ኢንሹራንስ እቅድ አማካኝነት ተጨማሪ አገልግሎቶች ማግኘታቸዉን ለማረጋገጥ የሚረዳ ሊሆን ይችላል። የሕክምና አቅራቢ የአይኤፍኤስፒ ወይም አይኢፒ ክፍል ያልሆኑ ሌሎች ቴራፒዎች እና አገልግሎቶችን ማዘዝ ይችላል።

ለልጆች 2 ዓመታቶ፣ 8 ወራቶች እድሜ እና ከዛ በላይ፣ ትምህርታዊ የኦተዝም ምደባ ኦቲዝምን በ አይዲኢኤ ስር እንደ እክል ለይቶ ያየዋል እና ለተለየ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁነትን ለይቶ ያዉቃል። ትምህርታዊ የኦቲዝም ምደባ ልጆች አስፈላጊ የሆነ ድጋፎችን ማግኘታቸዉን ለማረጋገጥ የሚረዳ ሊሆን ይችላል።

## ሁለቱንም የኦቲዝም ሕክምና ምርመራ እና ትምህርታዊ ምደባ መከተል አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት ምንድን ነዉ?

ቤተሰቦች በትምህርት ቤት ዉስጥ እና በማህበረሰብ ዉስጥ አገልግሎቶችን በተሻለ መልኩ ማግኘት ይችላሉ እና የልጃቸዉን እድገት ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ በይበልጥ ለመደገፍ ይችላሉ።

## እኔ ቀዳሚ ጣልቃገብነት/ትምህርታዊ ግምገማዎችን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

የእርስዎ ልጅ ዋና እንክብካቤ አቅራቢ ለ ጠንካራ አጀማመር ወይም ቀዳሚ ጣልቃ ገብነት ሊጠቁምዎት ወይም በእራስ-ጥቆማ ሊያደርጉ ይችላሉ።

- የእርስዎ ልጅ ከዉልደት እስከ 2 ዓመታቶች፣ 10 ወራቶች ከሆነ: **ጠንካራ አጀማመር ዲሲ ቀዳሚ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም** ክፍያ ነጻ መስመር (202) 727-3665 ላይ ይደዉሉ ወይም **ጥቆማ ቅጽ** ይሙሉ።
- የእርስዎ ልጅ 2 ዓመታቶች፣ 8 ወራቶች እና 5 ዓመታቶች፣ ወይም 10 ወራቶች ከሆነ: **ቀዳሚ ደረጃዎች** በ (202) 698-8037 ይደዉሉ ወይም እዚህ ጋር **ጥቆማ ቅጽ** ይሙሉ።

እባክዎትን ልብ ይበሉ ቀዳሚ ጣልቃገብነት/የተለየ ትምህርት ግምገማ ሂደት የሚጀምረዉ ወላጅ/አሳዳጊ የጽሁፍ ፍቃድ ሲሰጥ ብቻ ይሆናል።

### እኔ ልጄን ለኦቲዝም ሕክምና ምርመራ አገልግሎት እንዲያገኝ የምችለዉ የት ነዉ?

እርስዎ የኢንሹራንስ አቅራቢዎ ጋር መደወል ወይም የልጅዎ ሀኪም በመጠየቅ ኦቲዝም መመርመር የሚችል የሕክምና አገልግሎት የሚያገኙበትን ቦታ መጠየቅ ይችላሉ። ከዚህ በታች ኦቲዝምን የሚገመግሙ ክሊኒኮች ዝርዝር ይገኛል:

**ዲሲ ሜትሮ አካባቢ:**

- **ችልድረንስ ናሽናል ሆስፒታል: በርካታ የኦቲዝም ክሊኒኮች**
- **ሜድስታር ጆርጅታዉን ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል: ኦቲዝም ኤንድ ኮሚኒኬሽ ዲስኦርደርስ ክሊኒክ**
  202-444-2722

**ባልቲሞር አካባቢ:**

- **ሴንተር ፎር ኦቲዝም ኤንድ ሪሌትድ ዲስኦርደርስ በ ኬኔዲ ክሪገር ኢንስቲቲዩት**
  443-923-7630፣ አማራጭ 2
- **ኦቲዝም ስፔክትረም ሴንተር በ ማዉንት ዋሺንግተን ፒዲያትሪክ ሆስፒታል**
  410-367-2222

**የኦቲዝም ግምገማዎችን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ለወላጆች ምክር :**

- [x] የሕክምና ግምገማዎች መጠባበቂያ ዝርዝሮች ረዥም ናቸዉ (3 ወራቶች-2 ዓመታቶች)፣ ነገር ግን በዚህ ተስፋ አይቁረጡ
- [x] በርከት ያሉ ክሊኒኮች ጋር ይደዉሉ እና የጽሁፍ ማመልከቻ ያስገቡ፣ እርስዎ ቀጠሮ ካገኙ በኋላ በየትኛዉም ጊዜ በመደወል መሰረዝ ይችላሉ
- [x] የሕክምና ግምገማ እና ቀዳሚ ጣልቃገብነት/ትምህርታዊ ግምገማዎች በተመሳሳይ ወቅት ሊደረጉ ይችላሉ፣ እና አብዛኛዉ ጊዜ ላይ ሁለቱንም በተመሳሳይ ጊዜ ላይ መከተል ጥሩ ሀሳብ ነዉ
- [x] እርስዎ ያልገባዎት ነገር ካለ ጥያቄዎችን ይጠይቁ
- [x] አስፈላጊ ከሆነ ቀጣይ ምርመራ ግምገማዎችን ለማመቻቸት ከእርስ የሕክምና አቅራቢ ጋር አብረዉ ይስሩ

**እርስዎ እነዚህን አገልግሎቶች የማግኘት ወይም የማሰስ ሂደት ላይ ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነ፣ እነዚህን ያግኙ:**

- **አድቮኬትስ ፎር ጀስቲስ ኤንድ ኤዱኬሽን**
- **ቺልድረንስ ሎዉ ሴንተር**
- **ዲሲ ኦቲዝም ፓረንትስ**

የአሜሪካ ፔዲያትሪክስ አካዳሚ አቅርቦቶችን አዘጋጅቷል፣ **"ኦቲዝም የሚጠረጠር ከሆነ፣ በቀጣይ ምን ይሁን?"** ይህም በኦቲዝም ግምገማ ወቅት ምን እንደሚፈጠር መረጃ ያቀርባል፣ እንዲሁም የማይታዘዙ የሕክምና ምርመራዎች ዝርዝርም ያካትታል።

## ከግምገማ በኋላ ምን ማድረግ ነዉ ያለብኝ?

ወላጆች ከአቅራቢዎች እና ኤጀንሲዎች ጋር የሚያደርጉዋቸዉን ዉይይቶች እና ግንኙነቶች መዝገቦች መያዝ አለባቸዉ። ሴንተር ፎር ፓረንትስ ኢንፎርሜሽን ኤንድ ሪሶርስስ ይህን **ናሙና መዝገቦች መያዣ የስራ ሉህ** አዘጋጅቷል። ወላጆች የግምገማዉን ቅጂ ማግኘት እና ለልጃቸዉ ጤና እና ትምህርት አቅራቢዎች ማጋራት አለባቸዉ።

እንዲሁም ከሌሎች ኦቲዝም ከተመረመሩ ልጆች ወላጆች/ተንከባካቢዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር ጠቃሚ ይሆናል እና ከማህበረሰብ አቅርቦቶችን ማግኘትም ይጠቅማል። ይህን የብሎግ ልጥፍ ይመልከቱ ርዕሱ **“የእርስዎ ልጅ ኦቲዝም ምርመራ ከተደረገለት በቅድሚያ ማድረግ ያለብዎት ሶስት ነገሮች** መጀመሪያ ላይ ያግዝዎታል።

## ለቤተሰቦች የኦቲዝም አቅርቦቶች:

**ዲሲ ኦቲዝም ወላጆች(ዲሲኤፒ)** የ 501(ሐ)3፣ ወላጆች- በጎ ፍቃደኛ የሚመራ ለትርፍ-ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን የተመሰረተዉ ኦቲዝም ያለባቸዉ ልጆች ወላጆች ለኦቲዝም ያለባቸዉ ልጆች ወላጆች ነዉ። ዲሲኤፒ ወርሃዊ ዜናመጽሄት፣ የድጋፍ ቡድን ስልክ ጥሪዎች፣ እና ስልጠናዎችን ለወላጆች ያቀርባል። የእኛን ዜናመጽሄት ለማግኘት ምዝገባ ለማድረግ፣ እባክዎን ቀጣዩን ሊንክ ይጫኑ **እዚህ ጋር**።

የወላጆች ስልጠና እና መረጃ ማዕከል: እያንዳንዱ ግዛት ቢያንስ አንድ የወላጆች ስልጠና እና መረጃ (ፒቲአይ) ማዕከል አለዉ ይህም በ ኢንዲቪጂዋልስ ዊዝ ዲስኤቢሊቲስ ኢን ኤዱኬሽን አክት(አይዲኢኤ) ስር የገንዘብ ድጋፍ ይደረግለታል። የ ፒቲአይ አላማ ከዉልደት-22 ዓመት የሆኑ እክል ያለባቸዉ ልጆች ቤተሰቦችን የልጃቸዉን ትምህርት ደረጃ ከፍ ለማድረግ ነጻ መረጃ በመስጠት መደገፍ ነዉ። የዲሲ ፒቲአይ **አድቮኬትስ ፎር ጀስቲስ ኤንድ ኤዱኬሽን** ነዉ።

ፋሚሊ-ቱ-ፋሚሊ ሄልዝ ሴንተር (ኤፍ2ኤፍ): **አድቮኬትስ ፎር ጀስቲስ ኤንድ ኤዱኬሽን (ኤጀኢ)** የዲሲ ኤፍ2ኤፍ ነዉ፣ እነዚህም በ ሄልዝ ሪሶርስስ ኤንድ ሰርቪስስ አድሚኒስትሬሽን የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸዉ በቤተሰብ-የሚመሩ ማዕከሎች ናቸዉ። በእያንዳንዱ ግዛት ስር አንድ ኤፍ2ኤፍ ይገኛል፣ እና እያንዳንዱ ኤፍ2ኤፍ ከፍተኛ ክህሎት፣ እዉቀት ባላቸዉ የቤተሰብ አባላቶች አገልግሎት ይሰጣል፣ እነዚህ አባላቶች ቀጥተኛ-የሆነ ልምድ ያላቸዉ እና የተለየ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ያላቸዉ ሕጻናት እና ወጣቶች ቤተሰቦች የሚያጋጥማቸዉን ፈተናዎች የሚረዱ ናቸዉ።

**ፓረንት ቱ ፓረንት (ፒ2ፒ):** ፓረንት ቱ ፓረንት ዩኤስኤ የሀገር አቀፍ ፒ2ፒ ፕሮግራሞች ኔትወርክ ሲሆን ዓላማዉም እክሎች ያሉባቸዉ እና/ወይም የተለየ ጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ያላቸዉ ግለሰቦች ቤተሰቦች ጥራት ያለዉ ስሜታዊ ድጋፍ እንደሚያገኙ ማረጋገጥ ነዉ። በ አንድ-ለ-አንድ “ማዛመድ፣” ልምድ ያለዉ ድጋፍ ወላጆች የተለየ ጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ላላቸዉ ግለሰቦች ቤተሰቦች የስሜት ድጋፍ ያደርጉላቸዋል እና መረጃ እና አቅርቦቶች እንዲያገኙ እገዛ ያደርጋሉ። **ፋሚሊ ታይስ ኦፍ ዲሲ** የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ወላጆች እና እክል ላለባቸዉ ልጆች እንክብካቤ አድራጊዎች ወላጅ ለ ወላጅ ፕሮግራም ነዉ።

### ዴቨሎፕመንታል ዲስኤቢሊቲስ (ዲዲ) ካዉንስል:

**የዲሲ ዲዲ ካዉንስል** ገለልተኛ የሆነ፣ ማህበረሰብ-ላይ የተመሰረተ በ ዩ.ኤስ. ዲፓርትመንት ኦፍ ሄልዝ ኤንድ ሂዉማን ሰርቪስስ፣ አድሚኒስትሬሽን ኦን ኢንተለክቹዋል ኤን ዴቨሎፕመንታል ዲስኤቢሊቲስ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት አማካሪ ኮሚቴ ነዉ። የ ዲዲ ካውንስል የእድገት እክሎች ያሉባቸዉ ሰዎች እና ቤተሰቦችን ድምጽ ማጠንከር ይፈልጋል፣ በዚህም የጨመረ ራስ ገዝ፣ አካታች፣ ማብቃት፣ እና በመረጡት መልኩ ሕይወትን መከተል እንዲችሉ ያደርጋል።

ፓረንትስ ኢን ፓሊሲሜኪንግ (ፒአይፒ): ፒአይፒ የአእምሮ/እድገት እክሎች(አይ/ዲዲ) ያሉባቸዉ ጎልማሶች፣ ወላጆች፣ እና አይ/ዲዲ ያሉባቸዉ ልጆች እና ጎልማሶች ቤተሰብ አባላቶች የአካባቢ፣ ግዛት፣እና በፌደራል ደረጃ ዉጤታማ ተሟጋቾች እንዲሆኑ የሚያዘጋጅ ፕሮግራም ነዉ። ይህ ፕሮግራም በአሁኑ ወቅት ከ 30 በላይ ግዛቶች ዉስጥ ይገኛል፣ ይህም ዲሲ ያካትታል። **ዲሲ አድቮኬሲ ፓርትነርስ (ዲሲ ኤፒ)** የዲሲ ፒአይፒ ፕሮግራም ነዉ። ዲሲ ኤፒ የመሪነት ስልጠና ፕሮግራም ሲሆን የተዘጋጀዉ ለራስ-ተሟጋቾች እና አእምሮአዊ እና/ወይም እድገት እክሎች ያሉባቸዉ ሰዎች ቤተሰብ አባላቶች እንዲሁም እክል ካሉባቸዉ ሰዎች ጋር ለሚሰሩ ባለሙያዎች ታስቦ ነዉ።

DC AUTISM COLLABORATIVE

**የእድገት ክትትል፣ ማጣራት፣ እና ግምገማ ንዑስቡድን:**

ኢሚሊይ አሮን፣ አዜብ አዴሬ፣ ሻንተር አሌክሳንደር፣ ጄን አንደርሰን፣ ትሪና አንደርሰን፣ ራሄል ብሬዲይ፣ ቶሪ ብሮናዉህ፣ አይቪ ጊሴርማን-ኪስ፣ ሊአንድራ ጎዶይ፣ ዮላንዳ ግሬቭስ፣ ሳማንታ ሀምበርገር፣ አማንዳ ሀስቲንግስ፣ ዲያና ጃኮብስቴይን፣ ሻሊኒ ኩሁራና፣ ስቴሲ ላሞር፣ ቤኪይ ሌን፣ ሜሊሳ ሎንግ፣ ማይክል ሎንግ፣ ማይክል ሚንትዝ፣ የታ ማይሪክ፣ አላን ፊሊፕስ፣ ጆርዴን ሪደር፣ ካርላ ሪይድ-ዊት፣ ሊዝ ሪሃኒ፣ ካቲይ ሼይነር፣ አዉድሬይ ቱህርን፣ ያግናሽ ቫድጋማ፣ ሜሪ ዎዝኒያክ